# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org

## መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ሮሜ ፩

### ምዕራፍ ፩ ።

#### ክፍል ፩ ፣ በእንተ ጽዋዔሁ ።

፩ እምጳውሎስ ገብሩ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወሐዋርያ ዘተጸውዐ ወተፈልጠ ለትምህርተ ወንጌለ እግዚአብሔር ።

፪ ዘአቅደመ ነጊረ በአፈ ነቢያቲሁ ወመጻሕፍቲሁ ቅዱሳት ።

፫ በእንተ ወልዱ ዘተወልደ ወመጽአ እምዘርአ ዳዊት በሥጋ ሰብእ ።

፬ ወአርአየ ከመ ወልደ እግዚአብሔር ውእቱ በኃይሉ ወበመንፈሱ ቅዱስ በተንሥአቱ እሙታን ወውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚእነ ።

፭ ዘበቱ ረከብነ ጸጋ ወተሠየምነ ሐዋርያተ ከመ ናስምዖሙ ለአሕዛብ ወይእመኑ በስሙ ።

፮ ከመ አንትሙኒ ይእዜ ኮንክሙ ጽዉዓነ በኢየሱስ ክርስቶስ ።

#### ክፍል ፪ ፣ በእንተ ጽዉዓን ወበእንተ ሃይማኖቶሙ ።

፯ ለኵሎሙ እለ ሀለዉ ብሔረ ሮሜ ፍቁራኒሁ ለእግዚአብሔር ወኅሩያኒሁ ወቅዱሳኒሁ ሰላም ለክሙ ወጸጋ እግዚአብሔር አቡነ ወእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

፰ አቀድም አእኵቶቶ ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በእንተ ኵልክሙ እስመ ተሰምዐት ሃይማኖትክሙ ውስተ ኵሉ ዓለም ።

፱ ወእግዚአብሔር ሰማዕትየ ዘኪያሁ አመልክ በኵሉ መንፈስየ ወበትምህርተ ወልዱ ከመ እዜከረክሙ በጸሎትየ ዘልፈ ።

፲ ወእስእል ከመ ይሠርሐኒ እግዚአብሔር በፈቃዱ እምጻእ ኀቤክሙ ።

፲፩ እስመ እፈቅድ እርአይክሙ ወከመ ትርከቡ ጸጋሁ ለመንፈስ ቅዱስ ወበእንተዝ ከመ ይትፈጸሐ ልብክሙ እስመ ኀበርክሙ አሚነ ምስሌየ ።

#### ክፍል ፫ በእንተ ጻሕቀ መምህራን ወዕሤቶሙ ።

፲፪ ወእፈቅድ ባሕቱ ታእምሩ አኀዊነ ከመ ዘልፈ እፈቅድ እምጻእ ኀቤክሙ ወይሰአነኒ እስከ ይእዜ ።

፲፫ ወለእመኒቦ ከመ እርከብ ዕሤትየ በላዕሌክሙ ከመ በላዕለ አሕዛብኒ ።

፲፬ ወበላዕለ አረሚኒ ወበላዕለ ሐቃልኒ ወለጠቢባንኒ ወለዐብዳንኒ እስመ ይደልወኒ ለኵሉ ሰብእ እምሀር ።

## ከጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች የተላከ ፩

### ምዕራፍ ፩ ።

#### ክፍል ፩ ፣ ስለ መጠራቱ ።

የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማስተማር ተለይቶ ከተ ፩
ጠራው ሐዋርያ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ አገ
ልጋይ ከጳውሎስ የተላከ ። ግብ ሐዋ ፱ ፲፭ ፣ ፲፫ ፪ ።
በቅዱሳት መጻሕፍትና በነቢያት ቃል አስቀድሞ የተ ፪
ናገረ ። ምዕ ፲፮ ፳፭-፳፮ ። ቲቶ ፩ ፩ ።
ከዳዊት ዘር ሰው ሁኖ በሰው አካል ስለ ተወለደ ስለ ፫
ልጁ ። ምዕ ፱ ፭ ። ፪ ሳሙ ፯ ፲፪ ። ማቴ ፳፪ ፵፪-፵፮ ።
በከሃሊነቱ በጽኑ ሥልጣኑ ከሙታን ተለይቶ በመ ፬
ነሣቱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ስለ አሳየ
እሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። ዕብ ፱ ፲፬ ።
በስሙ እንዲያምኑ አሕዛብን ልናስተምር ሐዋርያትን ፭
የተሾምንበትንና ጸጋን ያገኘንበት ። ምዕ ፲፭ ፲፰ ።
ግብ ሐዋ ፱ ፲፭ ። ገላ ፪ ፯-፱ ።
እናንተም ዛሬ በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን የተጠራ ፮
ችሁ እንደመሆናችሁ ሁሉ ።

#### ክፍል ፪ ፣ ስለ አመኑትና ስለ እምነታቸው ።

በሮም ሀገር ላሉ እግዚአብሔር ለወደዳቸው ለመረ ፯
ጣቸውና ለአከበራቸው ሁሉ ትድረስ ሰላም የአባታ
ችን የእግዚአብሔር የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ
ጸጋም ለእናንተ ይሁንላችሁ ። ፩ ቆሮ ፩ ፪ ።
አስቀድሜ ስለ ሁላችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአ ፰
ብሔርን አመሰግነዋለሁ ሃይማኖታችሁ በዓለም ሁሉ
ተሰምታለችና ። ምዕ ፲፮ ፲፱ ። ፩ ተሰ ፩ ፰ ።
ዘወትር በምጸልየው ጸሎት እንዳስባችሁ ልጁ በአ ፱
ስተማረኝ ትምህርት በፍጹም ልቡናዬ የማመልከው
እግዚአብሔር ምስክሬ ነው ። ፊል ፩ ፫-፲ ፣ ኤፌ ፩ ፲፮ ።
ወደ እናንተም እመጣ ዘንድ እግዚአብሔር በፈቃዱ ፲
መንገዴን ያቀናልኝ ዘንድ እጸልያለሁ ። ምዕ ፲፭
፳፫ - ፴፪ ። ግብ ፲፱ ፳፩ ።
ከእኔ ጋር በሃይማኖት አንድ ስለ ሆናችሁ የመንፈስ ፲፩
ቅዱስንም ስጦታ እንድታገኙ ስለዚህም ልባችሁ
ደስ እንዲለው ላያችሁ እወዳለሁና ። ግብ ሐዋ ፳፰
፴፩ ። ፪ ጴጥ ፩ ፩ ።

#### ክፍል ፫ ፣ ስለ መምህራን ትጋትና ስለ ዋጋቸው ።

ግን ወንድሞቻችን፤ዘወትር ወደናንተ ልመጣ ስወድ ፲፪
እስከ ዛሬ እንደተሳነኝ ልታውቁ እወዳለሁ ።
አለኝ እንደሆነ በአሕዛብ ላይ እንዳገኘሁ በእናንተም ፲፫
ላይ ዋጋዬን አገኝ ዘንድ ። ምዕ ፲፭ ፳፫ ።
በአረመኔው ላይም ቢሆን ፣ በዘላኑ ላይም ቢሆን ፣ ፲፬
ለአዋቂዎችም ቢሆን ፣ ለሰነፎችም ቢሆን ሰውን ሁሉ
ላስተምር ይገባኛልና ።

፲፭ ወዓዲ ፈድፋደ እጽሕቅ ለክሙ ለእለ ብሔረ ሮሜ እምሀርክሙ ።

፲፮ እስመ ኢየኀፍር ምህሮ ወንጌሉ እስመ ኃይሉ ለእግዚአብሔር ውእቱ ዘያሐይዎሙ ለኵሎሙ እለ የአምኑ በቱ ፡ ለአይሁዳዊ ቀዳማዊ ወለአረማዊኒ ደኃራዊ ።

፲፯ ወበቱ ያስተርኢ ጽድቀ እግዚአብሔር ወርትዑ እስመ ያጸድቆሙ ለእለ የአምኑ በቱ በአሚን ፡ እስመ ከማሁ ይብል መጽሐፍ ጻድቅሰ በአሚን የሐዩ ።

<u>ክፍል ፩ ፡ በእንተ መቅሠፍት ዘይመጽእ ላዕለ ኃጥአን ።</u>

፲፰ ወይመጽእ መቅሠፍቱ እግዚአብሔር እምሰማይ ላዕለ ኵሉ ሰብእ ኃጥእ ወዐማፂ እለ የአምርዋ ለጽድቅ ወይመይጥዋ በዓመፃሆሙ ።

፲፱ እስመ አእምሮ እግዚአብሔር ክሡት በኀቤሆሙ ወአርአየ እግዚአብሔር ላዕሌሆሙ ።

፳ ወዘኢያስተርኢ እግዚአብሔር እምፍጥረተ ዓለም ይትዓወቅ በፍጥረቱ በሐልዮ ወበአእምሮ ወከመዝ ይትአመር ኃይሉ ወመለኮቱ ዘለዓለም ፡ ከመ ኢይርከቡ በዘይትዋሥኡ ።

፳፩ እስመ እንዘ የአምርዎ ለእግዚአብሔር አኮ ከመ እግዚአብሔር ዘአእኰትዎ ወሰብሕዎ ዘእንበለ ዘሐሰውዎ ወረኵሱ በሕሊናሆሙ ወተጸለለ ልበሙ ።

፳፪ ወእንዘ ይፈቅዱ ይጥበቡ ዓብዱ ።

፳፫ እስመ ወለጡ ስብሐቲሁ ለእግዚአብሔር ዘኢይመውት ወአምሳለ ርእየተ ሰብእ መዋቲ ረሰዩ ወከመ እንስሳ ወከመ አራዊት ወከመ አዕዋፍ ።

፳፬ ወበእንተዝ አግብአሙ ወኀደጎሙ ከመ ያርኵሱ ርእሶሙ ለሊሆሙ ወያኅሥሩ ነፍሶሙ ።

፳፭ እስመ ሐሰተ ረሰይዎ ለጽድቀ እግዚአብሔር ወአምለኩ ወተጸአጽኡ ተግባሮ ወኀደግዎ ለፈጣሬ ኵሉ ዘውእቱ አምላክ ቡሩክ ለዓለመ ዓለም አሜን ።

<u>ክፍል ፪ ፡ በእንተ እኩይ መቅሠፍት ።</u>

፳፮ ወበእንተዝ ወሀቦሙ እግዚአብሔር መቅሠፍተ እኩየ ወአንስቲያሆሙኒ ኃደጋ ፍጥረቶን ወተመሰላ በዘኢኮነ ፍጥረቶን ።

፳፯ ወከማሁ አደዊሆሙኒ ኀደጉ አንስቲያሆሙ ወነዱ በፍትወቶሙ ወገብኡ በበይናቲሆሙ ብእሲ ላዕለ ብእሲ ኀሣሮሙ ገብሩ ፡ ወበሕቱ ይረክቡ ፍዳሆሙ ወይገብእ ጌጋዮሙ ዲበ ርእሶሙ ።

፳፰ ወበከመ ኢሐለይዎ ለእግዚአብሔር በልበሙ ከማሁ

ይልቁንም በሮም ያላችሁ እናንተን ላስተምራችሁ አስብላችኋለሁ ። ፲፭

ጥንተ ገብ አይሁዳዊም ቢሆን ኋላ ገብ አረማዊም ቢሆን ያመኑበትን ሁሉ የሚያድናቸው የእግዚአብሔር ኃይሉ ስለሆነ ወንጌልን ማስተማር አላፍርምና ። ፲፮
መዝ ፻፲፱ ፵፮ ። ግብ ሐዋ ፲፫ ፵፮ ። ፩ ቆሮ ፩ ፲፰-፳፬ ።

እግዚአብሔር በውነት የሚያምኑበትን ስለሚያከብራቸው የእግዚአብሔር ቸርነቱና ቅን ፍርዱ በሱ ይገለጣል መጽሐፍ "ጻድቅ እኮ በሃይማኖት ይድናል" ብሎአልና ። ምዕ ፫ ፳፩-፳፪ ። እንባ ፪ ፬ ። ፲፯

<u>ክፍል ፩ ፡ በኃጥአን ላይ ስለሚመጣው መቅሠፍት ።</u>

እውነትን አውቀው በክፋታቸው በሚለውጧት በዓመፀኛው ሰው ላይ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መቅሠፍት ከሰማይ ይመጣል ። ፲፰

የእግዚአብሔርን ማወቅ በነሱ ዘንድ የተገለጠ ነውና እግዚአብሔርም ኃይሉን ገለጠባቸው ። ፲፱

ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ታይቶ የማይታወቅ እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት በማሰብ በመመርመር ይታወቃል ፡ ከሃሊነቱ የዘለዓለም ጌትነቱም እንዲህ ይታወቃል መልስ የሚሰጡበት ምክንያት እንዳያገኙ ። ፳

እግዚአብሔርን ሲያውቁት ካዱት እንጂ እንደ እግዚአብሔርነቱ አላመሰገኑትምና በገዛ አሳባቸው ረከሱ ልቦናቸውም ባለማወቅ ተሸፈነ ። ኤፌ ፬ ፲፰ ። ፳፩

እንራቀቃለን ሲሉ ሰነፉ ። ፩ ቆሮ ፩ ፳ ፣ ኤር ፲ ፲፬ ። ፳፪

የማይሞተውን የእግዚአብሔርን ክብር ለውጠዋልና የሚሞትም የሰው አምሳል አድርገዋልና የእንስሳ አምሳል የአራዊት አምሳል የአዕዋፍ አምሳል አድርገዋልና ዘዳግ ፬ ፲፭-፳፬ ። ፳፫

ስለዚህም ወደ ድንቍርና መለሳቸው በገዛ ራሳቸው እጃቸውም ራሳቸውን እንዲያረክሱ ሰውነታቸውንም እንዲያጐሰቍሉ ተለያቸው ። ግብ ሐዋ ፲፬ ፲፮ ። ፳፬

የእግዚአብሔርንም አምላክነት ሐሰት አድርገዉታልና ተዋርደው ፍጥረቱን አምልከዋልና ሁሉን የፈጠረውን ግን ተዉት ፡ ይኸውም በእውነት ለዘለዓለመ ዓለም የሚኖር አምላክ ነው ። መዝ ፸፮ ፳ ። ፳፭

<u>ክፍል ፪ ፡ ስለ ክፉ መቅሠፍት ።</u>

ስለዚህም እግዚአብሔር ክፉ መቅሠፍትን አመጣባቸው ሚስቶቻቸውም ሴትነታቸውን ተዉ ፡ ለሴትነት በሕርያቸው የማይገባውንም በመሥራት ተገኙ ፡ ዘሌ ፲፰ ፳፫ ። ፳፮

ወንዶቻቸውም እንዲሁ ሚስቶቻቸውን ተዉ በፍትወትም ተቃጠሉና እርስ በርሳቸው ተጋቡ ፤ አንዱ በአንዱ ላይ የሚያዋርዳቸውን ሥራ ሠሩ ግን ፍዳቸውን ያገኛሉ ፍዳቸውም በራሳቸው ይመለሳል ። ፳፯

እግዚአብሔርን በልቡናቸው እንዳላሰቡት መጠን ፳፰

፳፬ አከኑ በእንቲአነሂ እለ አመነ በዘአንሥኦ ለእግዚእነ
እሙታን ።
፳፭ ዘተሰቅለ በእንተ ኃጢአትነ ወተንሥአ ከመ ያንሥ
አነ ወከመ ያጽድቀነ ።

ምዕራፍ ፭ ።

## ክፍል ፳ ፥ በእንተ ጽድቀ ሃይማኖት ።

፩ ጽደቁ እንከ በአሚን ወንርከብ ሰላመ በኀበ እግዚአ
ብሔር በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

፪ ዘበእንቲአሁ ተመራሕነ በሃይማኖት ውስተ ዛቲ
ጸጋሁ እንተ ባቲ ቆምነ ወውእቱ ምክሕነ ወባቲ
ንሴፎ ስብሐተ እግዚአብሔር ።

፫ ወአኮ በባሕቲታ ዓዲ ንትሜከሕ በሕማምነሂ እስመ
ነአምር ከመ ሕማም ይፌጽም ትዕግሥተ ላዕሌነ ።

፬ ወትዕግሥትሰ መከራ ወበመከራ ይትረከብ ተስፉ ።
፭ ወተስፋኒ ኢያስተኀፍር እስመ ፍቅረ እግዚአብሔር
መልአ ውስተ ልብነ በመንፈስ ቅዱስ ዘወሀበነ ።

## ክፍል ፳ወ፩ ፥ በእንተ ምጽአተ ክርስቶስ ።

፮ ክርስቶስኒ መጽአ በዕድሜሁ ይሙት በእንተ ኃጢ
አትነ እንዘ ኃጥአን ንሕነ ።
፯ እንበይነ እኩያንሰ እምዕፁብ ጥቀ ኢይትረከብ ዘይ
ትሀበል ይሙት፥ ወእንበይነ ኄራንሰ እንዳዒ እንጋ
ለእመቦ ዘይትረከብ ዘያጠብዕ ይሙት ።
፰ ናሁ ርእዩ መጠነ አፍቀረነ እግዚአብሔር እንዘ ኃጥ
አን ንሕነ ክርስቶስ ሞተ በእንቲአነ ።

፱ እፎ እንከ ፈድፋደ ለእመ ጸደቅነ ያነጽሐነ በደሙ
ወያድኅነነ እመንሱት ዘይመጽእ ።

፲ ወሶበ እንዘ ፀሩ ንሕነ ለእግዚአብሔር ተሠሃለነ
በሞተ ወልዱ እፎ እንከ ይሠሀለነ ፈድፋደ ወእም
ከመ ተዓረቀነ ወተሠሀለነ ያሕይወነ በሕይወተ
ወልዱ ።
፲፩ አኮ በእንተ ዝንቱ ባሕቲቱ ዓዲ ንትሜካሕ በኀበ እግ
ዚአብሔር በእንተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘበ
እንቲአሁ ረከብነ ሣህሎ ።

## ክፍል ፳ወ፪ ፥ በእንተ ኃጢአት ዘቦአት ውስተ ዓለም ።

፲፪ ወበእንተዝ በከመ በኄጋየ አሐዱ ብእሲ ቦአት ኃጢ
አት ውስተ ዓለም በእንተ ይእቲ ኃጢአት መጽአ ሞት
ላዕለ ኵሉ ሰብእ ወተኀለቈት ኃጢአት ላዕለ ኵሉ ።



ጌታችን ከሙታን ለይቶ ባስነሣው ላመንና ስለኛም ፳፬
ነው እንጂ ። ግብ ሐዋ ፪ ፳፬ ።
ስለ ኃጢአታችን የተሰቀለውን ሊያስነሣን ሊያከ ፳፭
ብረን የተነሣውን ። ኢሳ ፶፫ ፬-፭ ። ፩ ቆሮ ፲፭ ፲፯ ።

ምዕራፍ ፭ ።

## ክፍል ፳ ፥ በሃይማኖት ስለሚገኘው ክብር ።

እንግዲህ በሃይማኖት ከበሩ በእግዚአብሔር ዘን ፩
ድም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰጪነት ዕርቅን
እናግኝ ። ኢሳ ፶፫ ፭ ። ዮሐ ፲፯ ፲፫ ።
ቤዛ ስለሆነ በሃይማኖት ወደ ጸናንበት ወደዚች ወደ ፪
ልጅነት የደረስንበት መመኪያችንም እሱ ነው ፥ በል
ጅነት እግዚአብሔር የሚሰጠንን ክብር ተስፋ እናደ
ርጋለን ። ኤፌ ፫ ፲፪ ።
የምንመካ በልጅነት ብቻ አይደለም በመከራችንም ፫
ደግሞ እንመካለን እንጂ መከራ በኛ ላይ ትዕግሥ
ትን ፍጹም እንደሚያደርገው እናውቃለንና ።
ትዕግሥት ፈተና ነው በፈተናም ተስፋ ይገኛል ። ፬
ተስፋም አያሳፍርም በሰጠን በመንፈስ ቅዱስ የእግ ፭
ዚአብሔር ፍቅር በልቡናችን መልቶአልና ። ፊል ፩
፳ ። ዕብ ፮ ፲፰-፲፱ ።

## ክፍል ፳፩ ፥ ስለ ክርስቶስ መምጣት ።

እኛ ኃጢአተኞች ስንሆን በኃጢአታችን ምክንያት ፮
ይሞት ዘንድ ክርስቶስ በቀጠሮው መጣ ።
ስለ ክፉዎችማ ሊሞት የሚደፍር በጭንቅ እንኳ ፯
ቢሆን የሚሞት አይገኝም ስለ ደጋጉ ሰዎች፥ ሊሞት
የሚደፍር እንዳለ እንጃ ። ዮሐ ፲፭ ፳፫ ።
አሁን እግዚአብሔር እንደወደደን እነሆ እዩ ፥ እኛ ፰
ኃጢአተኞች ስንሆን ክርስቶስ ስለኛ ሞተ ። ዮሐ ፫
፲፮-፳፩ ። ፩ ጴጥ ፫ ፲፰ ።
ጻድቃን ከሆንማ እንዴት በደሙ እጅግ ያነፃን! ፱
ከሚመጣው መከራስ እንደምን ያድነን ይሆን ? ።
ምዕ ፩ ፲፰ ። ፲፱ ፪-፰ ።
እኛ የእግዚአብሔር ጠላቶቹ ስንሆን በልጁ ሞት ፲
ይቅር ካለን እንደምን እጅግ ይቅር ይለን ይሆን ?
ይቅር ብሎ ከታረቀንም በልጁ ሕይወትነት ያድነ
ናል ። ምዕ ፰ ፯ ። ፪ ቆሮ ፭ ፲፰ ። ዮሐ ፲፬ ፲፱ ።
በዚህ ብቻ አይደለም ስለ ቤዛነቱ ይቅርታውን ባገኘ ፲፩
ንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስም በእግዚአብ
ሔር ዘንድ እንመካለን እንጂ ።

## ክፍል ፳፪ ፥ ወደ ዓለም ስለ ገባችው ኃጢአት ።

ስለዚህም በአንድ ሰው በደል ምክንያት ኃጢአት ፲፪
ወደ ዓለም እንደ ገባች ስለዚችም ኃጢአት በሰው
ሁሉ ላይ ሞት መጣ ፥ ኃጢአት በሁሉ ላይ ተቈ
ጠረች ። ምዕ ፮ ፳፫ ። ዘፍ ፪ ፲፯ ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፯ | አምኁ እንድራኒቆን ወዩልያን እለ አዝማድየ ወተዴወዉ ምስሌየ ወየአምርዎሙ ሐዋርያት ከመ ቀዲሙ ተልእኩ ለክርስቶስ ። | ከኔ ጋር በመከራ የተያዙ ከዘመዶቼ ወገን የሚሆኑ እንድራኒቆንና ዩልያንን እንዴት ናችሁ ? በሉ፡ ቀድሞም ከክርስቶስ እንደ ተማሩ ሐዋርያት ያውቋቸዋል ። ፪ ቆሮ ፰ ፳፫ ። | ፯ |
| ፰ | አምኁ ጵልያጦን እኁየ በክርስቶስ ። | ክርስቶስን በማመን ወንድሜ የሚሆን ጵልያጦንን እንዴት ነህ ? በሉ ። | ፰ |
| ፱ | አምኁ ኡሩባኖን ዘኅንብር በግብረ ክርስቶስ ወስንጣክን እኁየ ። | በክርስቶስ ሥራ አንድ የምንሆን ኡሩባኖንን ወንድሜ ስንጣክንን እንዴት ናችሁ ? በሉ ። | ፱ |
| ፲ | አምኁ ኤጤሌን ኅሩየ ለክርስቶስ ፣ አምኅዎሙ ለእለ አርስጠቦሉ ። | ክርስቶስ የመረጠው ኤጤሌንን እንዴት ነህ ? በሉ ፣ የአርስጠቦሉንም ወገን እንዴት ናችሁ ? በሏቸው ። | ፲ |
| ፲፩ | አምኁ ሄሮድያና ዘእምአዝማድየ ፡ አምኁ እለ እምውስተ ቤተ ንርቃሱ እለ በክርስቶስ ። | ከዘመዶቼ ወገን የሚሆን ሄሮድያናን እንዴት ነህ ? በሉ ፡ በክርስቶስ ያመኑ የንርቃሱን ወገን እንዴት ናችሁ ? በሉ ። | ፲፩ |
| ፲፪ | አምኁ እለ ጢሮፊሞና ወጢሮፊሞስ እለ ፃመዉ በእግዚእን ፡ አምኁ ጠርሲዳ እኅትነ እንተ ብዙኀ ፃመወት በእግዚእን ። | በጌታችን አምነው መከራ የተቀበሉ ጥሮፊሞንና ጢሮፊሞስ እንዴት ናችሁ ? በሉ ፤ ስለ ጌታችን ብዙ መከራ የተቀበለች ጠርሲዳን እንዴት ነሽ ? በሉ ። | ፲፪ |
| ፲፫ | አምኁ ሮፎን ኅሩየ ለእግዚእን ፡ ወእሞ ወሊተኒ እምየ ። | ጌታችን የመረጠው ሮፎንን የኔንና የሱንም እናት እንዴት ናችሁ ? በሉ ። ማር ፲፭ ፳፩ ። | ፲፫ |
| ፲፬ | አምኁ አስቀሪጦን ወአፍልሶንጳ ወሄርሜን ወጳጥሮባን ወሄርማን ወአኀዊነ እለ ምስሌሆሙ ። | ለአስቀሬጦንና ለአፍልሶንጳ ለሄርሜንም ለጳጥሮባን ለሄርማንም ከእነርሱም ጋር ላሉ ወንድሞች እንዴት ናችሁ? በሉ ። | ፲፬ |
| ፲፭ | አምኁ ፊልጎን ወዩልያ ወኔርያ ወእኅቶ ወአልንጦን ወኵሎሙ ቅዱሳነ ምስሌሆሙ ። | ለፊሉጎንና ለዩልያ ለኔርያና ለእኅቱም ለአልንጦንም ከእነርሱም ጋር ላሉ ቅዱሳን ሁሉ እንዴት ናችሁ? በሉ ። | ፲፭ |
| ፲፮ | ወተአምኁ በበይናቲክሙ በአምኃ ቅድሳት ፡ ወአምኁክሙ ኵሉ አብያተ ክርስቲያናቲሁ ለክርስቶስ ። | በተቀደሰ ሰላምታ እርስ በርሳችሁ እንዴት ናችሁ ? ተባባሉ ፡ በክርስቶስ ያመኑ ምእመናን ሁሉ እንዴት ናችሁ ? ይሏችኋል ። ፩ ቆሮ ፲፮ ፳ ። | ፲፮ |
| ፲፯ | አስተበቍዐክሙ አኃዊነ ተዓቀብዎሙ ለእለ ይገብሩ ሀከከ ወያመጽኡ ካሕደ ላዕለ ትምህርትክሙ ዘተመሀርክሙ ትግበሩ በቲ ወተገኀሥዎሙ ። | ወንድሞቻችን ! ጸብ ክርክር የሚያደርጉትን በተማራችሁት ትምህርት ላይ ክሕደትን የሚያመጡትን ሰዎች ተጠባበቍአቸው ብዬ እማልዳችኋለሁ ፤ ተለይዋቸው ። ማቴ ፯ ፲ ። ቲቶ ፫ ፲ ። | ፲፯ |
| ፲፰ | እስመ ለክርሦሙ ይትቀነዩ ወአኮ ለእግዚእን ኢየሱስ ክርስቶስ ፡ ወበኂጣነ ነገር ወበተየውሆ ያስሕትዎሙ ለብዙኃን የዋሃን ። | ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ያይደለ ለሆዳቸው ይገዛሉና ፡ በነገር ማታለል የዋህ በመምሰል ብዙዎቹን የዋሆች ያስታሉ ። ሕዝ ፲፫ ፲፰ ፤ ፊል ፫ ፲፱ ፤ ቈላ ፪ ፬ ። | ፲፰ |
| ፲፱ | ወነገረ ዚአክሙሰ ተሰምዐ በኵለሄ ወእትፌሣሕ በእንቲአክሙ ፣ ወእፈቅድ ለክሙ ትጥበቡ ለሠናይ ወትትገኀሠዎ ለእኩይ ። | የእናንተ ወሬ በሁሉ ዘንድ ተሰምቷል ፡ ስለ እናንተም ደስ ይለኛል ፣ ክፋውን ትታችሁ ለበጎ ነገር አዋቆች ትሆኑ ዘንድ እወዳለሁ ። | ፲፱ |
| ፳ | ወአምላከ ሰላም ይቀጥቅጦ ለሰይጣን በታሕተ እገሪክሙ ፍጡነ ፡ ጸጋሁ ለእግዚእን ኢየሱስ ክርስቶስ የሀሉ ምስሌክሙ ። | የሰላም ባለቤት እግዚአብሔር ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ይጣለው ፣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ይደርባችሁ ። | ፳ |
| ፳፩ | ይኤምኃክሙ ጢሞቴዎስ ዘኅንብር ግብረ ምስሌሁ ወሉቅዮስ ወኢያሶን ወሱሲ ጴጥሮስ እለ እም አዝማድየ ። | በሥራ ከእርሱ ጋር አንድ የምንሆን ጢሞቴዎስ፣ ከዘመዶቼም ወገን የሚሆኑ ሉቅዮስ ኢያሶን ሱሲጴጥሮስ እንዴት ናችሁ ? ይሏችኋል ። ግ ሐ ፲፮ ፩-፪ ፡ ፊል ፪ ፲፱ ። | ፳፩ |
| ፳፪ | ወእማኅኩክሙ አነ ጤርጥዮስ ዘጸሐፍክዋ ለዛቲ መጽሐፍ በእግዚእን ። | ይህችን መልእክት የጻፍሁ እኔ ጤርጥዮስ በጌታችን ሰላምታ እንዴት ናችሁ ? እላችኋለሁ ። | ፳፪ |
| ፳፫ | አምኃክሙ ጋይዮስ ዘያኃድረኒ በንግደትየ ፡ ወኵሉ | በእንግድነቴ ጊዜ ያሳደረኝ ጋይዮስ እንዴት ናችሁ ? | ፳፫ |

አብያተ ክርስቲያናት ፡ አምኁክሙ አርስጦስ መጋቤ
ሀገር ወቊአስጥሮስ እኁነ ።

፳፭ ውእቱ ዘይክል ያዕንዕክሙ እግዚአብሔር ላዕለ ስብ
ብከት ዘእሰብክ ባቲ በእንተ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘኅ
ቡእ ኅርመታ እምቅድመ ዓለም ።

፳፮ ወአስተርአየ በዝ መዋዕል እምቃለ ነቢያት ወበትእ
ዛዘ እግዚአብሔር ዘለዓለም ከመ ይስምዑ ኵሉ አሕ
ዛብ ወይእመኑ በኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአ
ብሔር ።

፳፯ ወያእምርዎ ለእግዚአብሔር ዘሎቱ ስብሐት ወውእቱ
ጠቢብ ለዓለመ ዓለም ፡ አሜን ።

፳፯ ጸጋሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ የሃሉ ምስለ
ኵልክሙ ፡ አሜን ።

ተፈጸመት መልእክት ኅበ ሰብአ ሮሜ ፡ ዘተጽሕፈት በቆሮንቶስ ወተፈነወት በእደ ፌቤን እንተ ትትለአከሙ ለቤተ ክርስቲያን ዘክንክርኤስ ፡ ወስብሐት ለእግዚአብሔር ለዓለመ ዓለም ፡ አሜን ።



ይላችኋል ፡ ምእመናንም ሁሉ እንዴት ናችሁ?
ይሏችኋል፡ አገር አሳዳሪ አርስጦስና ወንድማችን
ቊአስጥሮስ እንዴት ናችሁ? ብለዋችኋል ። ፩ ቆሮ
፩ ፲፬ ። ግብ ሐዋ ፲፱ ፳፪ ።
ከዓለም አስቀድሞ ምሥጢሩ ተሠውሮ ስለ ነበረ ፳፭
ኢየሱስ ክርስቶስ በማስተምራት ትምህርት ላይ ሊያ
ፀናችሁ የሚቻለው እሱ እግዚአብሔር ነው ። ኤፌ
፩ ፱ ፡ ፫ ፱ ።
በነቢያት ቃልና የዘለዓለም ገዢ በሚሆን በእግዚአ ፳፮
ብሔር ትእዛዝ በዚህ ወራት ተገለጠ ፡ አሕዛብ ሁሉ
ይህን ሰምተው በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክር
ስቶስ ያምኑ ዘንድ ።
ምስጋና የሚገባው ለዘለዓለሙ ዐዋቂ የሚሆን እግ ፳፯
ዚአብሔርን ያውቁት ዘንድ ። ፩ ጢሞ ፩ ፲፯፤
ይሁ ፳፭ ።
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ፳፯
ይሁን፤ ያለ ሐሰት በውነት ።

በቆሮንቶስ ተጽፋ ለክንክርኤስ ማኅበረ ክርስቲያን በምትላከው በፌቤን እጅ ወደ ሮሜ ሰዎች የተላከችው መልእክት ተፈጸመች፤ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ፡ ለዘለዓለሙ አሜን ።